DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# የደረጃ ሁለት መመሪያ
## Coronavirus2019(COVID-19): ለሕዝብ መጓጓዣዎች የሚሆን መመሪያ

በደረጃ ሁለት ወቅት ፣ ህዝብ እና ቢዝነሶች ለሁሉም የተጋላጭነትን እድል ለመቀነስ አዳዲስ ባህሪያትን እና ጠንከር ያሉ የደህንነት እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ ። በሠራተኞች ፣ በደንበኞች እና በማህበረሰቡ መካከል የ COVID-19 የስርጭት አደጋን ለመቀነስ የሚከተሉት እርምጃዎች መተግበር አለባቸው ። ለተጨማሪ መረጃ coronavirus.dc.gov/phasetwo. ን ይመልከቱ።

እባክዎን ያስተውሉ የ COVID-19 ምልክቶች የሚታዩበት ወይም በቅርብ ጊዜ በ COVID-19 ከተያዘ ሰው ጋር ግኑኝነት ያደረገ ማንኛውም ግለሰብ፤ ሌሎችንም ለበሽታው የማጋለጥ እድል ስላለው የሕዝብ መጓጓዣን መጠቀም የለበትም ። የ COVID-19 ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ: ትኩሳት (በግምት ወይም 100.4 ዲግሪ ፋራናይት) ፣ ብርድ-ብርድ ማለት ፣ ሳል ፣ የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር ፣ ድካም ፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመም ፣ ራስ ምታት ፣ አዲስ የጣዕም ወይም የሽታ ስሜት ማጣት ፣ የጉሮሮ መቁሰል ፣ የአፍንጫ መደፈን ወይም ፈሳሽ፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ ፣ ተቅማጥ ፣ ወይም ደግሞ ጥሩ ያልሆነ የጤና ስሜት።

### ደረጃ ሁለት ለሕዝብ መጓጓዣዎች መስተዳድር የሚሆን አጠቃላይ አትኩሮት

- ወደ ሥራ እና ወደ ት/ ቤት የሚደረገውን ጉዞ ለማሳደግ የሕዝብ መጓጓዣ አገልግሎቶች ፍላጎቶችን ለማሟላት በቀጣይነት መስራት አለባቸው ።
- ለላይፍ-ላይን የአውታረመረብ አውቶቢስ ኮሪደሮች የመሄጃ መስመሮችን መመደብ እና ለምልክቶች ስፍራ መስጠት።
- የስኪፐ-ስቶፕ አገልግሎትን በቀጣይነት መስጠት።
- ከፍተኛ አገልግሎት ወደሚሰጣቸው አካባቢዎች የአውቶቢስ መሄጃ መንገዶችን መቀየር ወይም ቅድሚያ መስጠት።
- በ WMATA በኩል ያለ ንክኪ እና የተቀናጀ የትራንስፖርት ክፍያዎችን ጨምሮ ጠቅላላ ጉዞዎችን እና የተቀናጁ የጉዞ ሁኔታዎችን ማዘጋጀት ።

### ሰራተኞች እና ደንበኞች በየቀኑ የመከላከያ እርምጃዎችን መለማመድ አለባቸው

- **ከታመሙ** ወይም በቅርብ ጊዜ በ COVID-19 ከተያዘ ሰዉ ጋር ከተገናኙ **ቤት ይቆዩ**።
- የህብረተሰብ አባላት ያለቦት ለአስፈላጊ ጉዳይ ካልሆነ በስተቀር የታመሙ ከሆነ የህዝብ መጓጓዣን አይጠቀሙ።
- በሚቻልበት ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ቢያንስ የ 6 ጫማ ያህል ርቀትን ይጠብቁ።
- ሰራተኞች እና ደንበኞች በሁሉም ጊዜ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ ማድረግ አለባቸው።
- ደንበኞች የራሳቸውን ሻንጣ መያዝ እና በሚቻልበትም ጊዜ ንክኪ የሌላቸውን የክፍያ አማራጮችን መጠቀም አለባቸው።
- በተደጋጋሚ የእጅ ንጽሕናን ያከናውኑ (በሳሙና እና በውኃ ወይም የአልኮል ይዘት ባለው የእጅ ማፅጃ ሳይኒታይዘር) ።
    - የእጅ ንፅህናን ለማከናወን ቁልፍ ጊዜዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:
        - ምግብ ከመመገብ በፊት፣
        - መጸዳጃ ቤት ከመጠቀም በፊት እና በኋላ፣
        - የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ከመልበስዎ፣ ከመንካትዎ ወይም ከማዉለቅዎ በፊት እና በኋላ፣
        - ከስራ ፈረቃ እና የስራ ዕረፍት በፊት እና በኋላ፣
        - ገንዘብ ከያዙ / ከተለዋወጡ በኋላ ፣
        - ነዳጅ ከመሙላት በፊትና በኃላ
        - ማስቀረት የማይቻል ከሆነ የደንበኞችን የግል ንብረቶች ከያዙ በኋላ ፣እና
        - አፍንጫዎን ካፀዱ፣ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ በኋላ።
- የመጓጓዣ ኦፕሬተሮች ቲሹዎችን በአውቶቢሱ / በባቡሩ ኮክ-ፒት ውስጥ መያዝ አለባቸው ። ኦፕሬተሮች እና ደንበኞች በተሽከርካሪ ውስጥ በሚያስሉበት ወይም በሚያስነጥሱበት ጊዜ አፍና አፍንጫቸውን መሸፈን፣ የእጅ ንጽሕናን ማከናወን እና ሶፍቱን በቆሻሻ መጣያ ውስጥ መጣል።
- ጓንት መደረግ ያለበት በመደበኛው የሥራ ኃላፊነት ላይ በተጠቀሰው መሠረት ብቻ ነው።
- ደንበኞች የደህንነት እርምጃዎችን ለማክበር አሻፈረኝ ካሉ ይህን ጉዳይ ለአስተዳደር እና / ወይም ለባለሥልጣናት ሪፖርት ማድረግ ይችላሉ ።
- ለደህንነት ሲባል በሚታይ ሁኔታ ታማሚ ለሆኑ ደንበኞች የትራንስፖርት አገልግሎትን ለማቅረብ ምቾት የማይሰማዎ ከሆነ አገልግሎቱን አለመስጠት ይችላሉ ። ቢሆንም ግን በዘር ፣ የትውልድ ሀገር ፣ ወይም በሌሎች ምክንያቶች በኩባንያዎ

ፖሊሲዎች ፣ በአካባቢያዊ ፣ በስቴት እና በፌዴራል ሕግ በተገለፀው መሠረት በደንበኞች ላይ የሚደረግ አድልዎ በጥብቅ የተከለከለ ነው ::

## የሰራተኛ እና የደንበኛ ደህንነት ለማበረታታት የሚሆን የአሰሪ አትኩሮት

- በመጓጓዣ ተሸከርካሪዎች ፣ በሥራ ቦታዎች እና በጋራ ቦታዎች ውስጥ በተደጋጋሚ የእጅ ንጽህና እንዲተገበር (ለምሳሌ: ሳሙና እና ውኃ ወይም 60% የአልኮል ይዘት ያለውን የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር) ለሠራተኞቹ አቅርቦቶችን ያዘጋጁ ::
- በትራንዚት-ሃብ መግቢያዎች እና የጋራ ቦታዎች ላይ የእጅ ንፅህና መጠበቂያ ጣቢያዎችን ማዘጋጀት ::
- ለሠራተኞች ተገቢን የግል መከላከያ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ: ጭምብሎች ፣ ጓንቶች) እና የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ያቅርቡ ::
- ተለዋዋጭ እና ቅጣትን የማያሳዩ የፈቃድ ፖሊሲዎችን ይተግብሩ ፣ እንዲሁም የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ ይፍቀዱላቸዉ::
  - የትምህርት ቤት ወይም የሕፃናት መንከባከቢያ ስፍራዎች መዘጋት ያሉባቸው እነደሆነ ፣ ወይም የታመሙ የቤተሰብ አባሎቻቸውን የሚንከባከቡ ከሆነ ከልጆቻቸው ጋር አብረው መቆየት ለሚፈልጉ ሰራተኞች ደግሞ የፈቃድ ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆን አለባቸው::
- በተቻለ መጠን ፈረቃዎችን ፣ የመጀመሪያ ሰዓቶችን እና የእረፍት ጊዜዎችን መመደብ::
- በመጓጓዣው ኦፕሬተሮች እና በደንበኞች መካከል ያለውን የቅርብ ግኑኝነት እና የእቃ መጋራትን የሚገድቡ ወይም የሚያስቀሩ ያለ ንክኪ የሚደረጉ ግብይቶችን ለማድረግ የሚያስችሉ እና ቅድሚያ የሚሰጡ ፖሊሲዎችን እና የቴክኖሎጂ አማራጮችን ያዳብሩ ::
- ተቀጣሪዎችን ስለ COVID-19 ማስተማር:: ለበለጠ መረጃ https://coronavirus.dc.gov/ ይህንን ይጎብኙ።
- ለአውቶቡሶች እና ለሕዝብ መጓጓዣዎች የተለየ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላት (CDC) ን ድረ ገጽ ይመልከቱ: https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/worker-safety-support/index.html

## ለበሽታው ምልከቶች ማጣራት እና መከታተል

- የመንግሥት መጓጓዣ አስተዳደር በየቀኑ ሰራተኞቹ የስራ ፈረቃቸውን ከመጀመራቸው በፊት በስልክ ወይም በአካል በመገኘት የሚደረግ ምርመራ (ለምሳሌ: የምልክት መጠይቅ) ማከናወን አለበት ::
- የምርመራ ሂደቶችን ለሠራተኞቹ ለማሳወቅ በሠራተኞቹ መግቢያ ላይ ምልክት ያስቀምጡ ::

- አንድ ሠራተኛ በስራ ቀን ላይ እያለ ማንኛውንም የ COVID-19 ምልክት ያሳየ እንደሆነ ፣ ያ ግለሰብ ወዲያውኑ ራሱን የሚያገልበት፣ ለአለቃው የሚያሳውቅበት እና የደንበኞችን የማጓጓዝ አገልገሎት አቁሞ እና / ወይም አገልግሎቱን ትቶ መውጣት የሚችልበት ሂደት ተዘጋጅቶ መቀመጥ አለበት::

## የቅርብ ግንኙነትን ያስወግዱ እንዲሁም የመነካከያ ስፍራዎችን ይቀንሱ

- በደንበኞች በተደጋጋሚ ከሚነካኩ ቦታዎች ጋር ንክኪ ከማድረግ ይቆጠቡ :: በሰውነት ፈሳሾች የተበከሉ ቦታዎችን ለመንካት ከፈለጉ ጓንትን ይጠቀሙ
- አካላዊ ርቀት እንዲኖር ማድረግ:: በባቡሮች እና በአውቶቢሶች ላይ ያሉትን የመሃል መቀመጫ ቦታዎችን ማስቀረት ወይም ካልሆነ ደግሞ የአካላዊ ርቀት መመሪያዎችን ለመጠበቅ ቀጥታ አጠገብ ለአጠገብ እንዳይቀመጡ በሚያስችል መልኩ ደንበኞችን ማስቀመጥ::
- ለአውቶቢስ አሽከርካሪዎች:
  - የአውቶቢሱ ደንበኞች በኋለኞቹ የመግቢያ በሮች እንዲገቡና እንዲወጡ መጠየቅን ከግንዛቤ ማስገባት እንዲሁም ደንበኞች ከአውቶቢሱ ሾፌር በ 6 ጫማ ርቀት ውስጥ መቆምም ሆነ መቀመጥ እንደሌለባቸው ማሳሰብ
  - በመጫኛ እና በማዉረጃ ጊዜ ደንበኞች የራሳቸውን የግል ሻንጣዎች እና ንብረቶቻቸውን እንዲይዙ መጠየቅን ከግንዛቤ ማስገባት:: ይህ የማይቻል ከሆነ ደግሞ የእጅን ንፅህና መጠበቅ
- ለአውቶቢሶች: በአውቶቢሱ ሾፌር እና በደንበኞች መካከል ከ 6 ጫማ በላይ የሆነ ርቀት እንዲኖር በአካል መለየትም ሆነ በማስገደድ ተቋሙ እርምጃዎችን ይወስዳል:: እነዚህም የሚያካትቱት የአካል መለያዎችን ወይም የሚታዩ ምልክቶችን ጥቅም (ለምሳሌ: ወለል ላይ የሚለጠፉ፣ ባለቀለም ቴፕ ፣ ወይም በአውቶቢሱ ሾፌር አካባቢ የት ጋር መቆም እንዳለባቸው ወይም እንደሌለባቸው የሚጠቁሙ ምልክቶች)ላይ መዋል ነው።

## ማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ማድረግ

- የሕዝብ መጓጓዣ አስተዳደር ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት እና ከፍተኛ ንክኪ የሚደረግባቸውን ቦታዎች (ለምሳሌ: ቆጣሪዎችን ፣ የክፍያ መገልገያዎችን ፣ መጸዳጃ ቤቶችን ፣ ወዘተ) ቀኑን ሙሉ በተደጋጋሚ ለማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ለማድረግ አጠቃላይ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል ።
- አብዛኛውን ጊዜ በኦፕሬተሩ የሚነካኩ ነገሮች እንዲጸዱ ከጀርም ነፃ ማድረጊያ ስፕሬይ ወይም ሊወገዱ የሚችሉ ማጽጃዎች እና የቆሻሻ መጣያ ከረጢቶች በአውቶቢሱ / በባቡሩ ኮክ-ፒት ውስጥ መኖር አለባቸው ። ከፀረ-ተዋህሲያኑን የምርት ወረቀት ላይ አጠቃቀሙን መከተል።
- ወለሎቹ በሚታይ መልኩ ቆሻሻ ከሆኑ ከጀርም ነፃ ከማድረግ በፊት በሳሙና ምርቶች ወይም ሳሙና እና ውኃን በመጠቀም መጸዳት አለባቸው።
- በትንሹ፣ በእያንዳንዱ ፈረቃ መጀመሪያ እና መጨረሻ ላይ በመጓጓዣ ተሽከርካሪዎች ውስጥ አብዛኛውን ጊዜ የሚነካኩ ነገሮችን ማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ማድረግ።
- መርሐግብሩ በፈረቃዎች መካከል ለማፅዳት እና ከጀርም ነፃ ለማድረግ በቂ ጊዜ እንዲኖር የሚያስችል መሆን አለበት ።
- COVID-19 ን የሚያስከትለውን ቫይረስ ለማጥፋት ውጤታማ ስለሆኑ ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረጊያ ምርቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ድረ ገጽ https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/reopen-guidance.html ን ይመልከቱ።
- የመጓጓዣ አገልግሎት ተቋሙ የቢሮ ቦታዎችን ስለ ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ስለ ማድረግ የበለጠ መረጃ ለማግኘት https://www.cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/reopen-guidance.html ን ይመልከቱ።

## ለ COVID-19 የመጋለጥ አደጋ ወቅት የሚረዱ እቅዶችን ማዘጋጀት

- አንድ ሰራተኛ በ COVID-19 በሚያዝበት አጋጣሚ ወቅት ሊደረጉ ስለሚገቡ ነገሮች እቅድ ያውጡ።
- በስራ ቦታው ውስጥ ያለ አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ እና ይህን መረጃ ማሳወቅ ከፈለገ ሊያሳውቅ የሚችልበትን የመገናኛ ስፍራን ለይቶ ማዘጋጀት።
- አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ እንደሆነ ለስራ ቦታው ለማሳወቅ ከወሰነ፣ የስራ ቦታው የሚከተሉትን ለሰራተኞቹ ለማጋራት የማሳወቂያ ሂደት ሊኖረው ይገባል፡
  - የ COVID-19 ፍንጮች እና ምልክቶችን ጨምሮ ስለ COVID-19 ትምህርት መስጠት
  - ለ COVID-19 የምርመራ ውጤት ፖዘቲቭ ለሆኑ ግለሰቦች የግኑኝነት መረጃ መመሪያ ማየት ከፈለጉ በ coronavirus.dc.gov ላይ ይገኛል።
  - በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ለ COVID-19 ምርመራ አማራጮች መረጃ በ coronavirus.dc.gov/testing ይገኛል።
- አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ እንደሆነ ለስራ ቦታው ካሳወቀ፣ **እና** ሰራተኛው ከደንበኞች ጋር የቅርብ ግንኙነት አድርጎ ከነበር **<u>ወይም</u>** ደንበኞች የ COVID-19 የምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ እንደሆነ ለስራ ቦታው ካሳወቁ፣ የስራ ቦታው ከሚከተለው መረጃ ጋር በ coronavirus@dc.gov ላይ በኢሜይል ለዲሲ ሄልዝ ማሳወቅ አለበት:
  - በኢሜይል የርዕሰ ጉዳዩ መስመር ላይ “COVID-19 ኮንሳልት”
  - ዲሲ ሄልዝ ጥሪውን ለመመለስ እንዲያስችለዉ በስራ ቦታው ዉስጥ ጥሩ የሚባል የማግኛ ቦታ ስም እና የቀጥታ ስልክ ቁጥር
  - ተጋልጠዋል ተብለው የሚታሰቡ ደንበኞች ግምታዊ ቁጥር
  - ስለ ክስተቱ / ሁኔታው የሚገልጽ አጭር ማጠቃለያ
- የዲሲ ሄልዝ የምርመራ ባለሙያ በ 48 ሰዓታት ውስጥ በተገቢው መንገድ የቀረቡትን የኢሜይል ማስታወቂያዎችን የሚከታተል ይሆናል።

ከዚህ በላይ ያሉት መመሪያዎች ወረርሽኙ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር እየተሻሻሉ የሚቀጥሉ ይሆናሉ። እባክዎን https://coronavirus.dc.gov/ ን ለወቅታዊ መረጃ በመደበኛነት ይጎብኙ።